የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ቁጥር አ1162/11/784

ቀን ኅዳር 21 ቀን 2015 ዓ.ም.

**ለሲዳማ አርነት ንቅናቄ (ሲአን)**

**ሀዋሣ፣**

**ጉዳዩ፡- የቦርዱን ውሣኔ ማሳወቅ፤**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ግንቦት 12/2014 ዓ.ም. የሲዳማ አርነት ንቅናቄ (ሲአን) ጠቅላላ ጉባኤውን እስከ ሐምሌ 23/2014 ዓ.ም. ድረስ እንዲያደርግ ወስኖ ግንቦት 22/2014 ዓ.ም. በቁጥር አ1162/11/625 በተፃፈ ደብዳቤ አስታውቋል፡፡

ፓርቲው በቦርዱ ውሣኔ መሠረት ጠቅላላ ጉባኤውን ለመጥራት እንዲያስችለው በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ ማሻሻያ ለማድረግ የማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ማድረጉንና፤ በዚህም ስብሰባ ጠቅላላ ጉባኤ ለመጥራት ሊቀመንበሩ ወይም ምክትል ሊቀመንበሩ ከሌሉ ዋና ፀሐፊው በጽሕፈት ቤት ኃላፊው አቅራቢነት በሥራ አስፈፃሚ አፀድቆ ጠቅላላ ጉባኤ መጥራት እንዲችል ወስኗል በማለት ይህ የማዕከላዊ ኮሚቴ ውሣኔ እንዲፀድቅ ጥቅምት 3 ቀን 2015 ዓ.ም. በቁጥር ሲአን02/15 ለቦርዱ ፓርቲው በፃፈው ደብዳቤ ጥያቄ አቅርቧል፡፡

በሌላ በኩል 23 የሚሆኑ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላቱ ከ2010 ዓ.ም. ወይም ከ2011 ዓ.ም. ወይም ከ2012 ዓ.ም. ጀምሮ ስብሰባ ተሳትፈው የማያውቁ በመሆኑ ከማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነት የተሰረዙ ናቸው በማለት ለቦርዱ አሳውቋል፡፡ ከዚህ ውጭ ተጨማሪ 28 የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ከአባልነት የተሰረዙ ናቸው በሚል በተላከው ዝርዝር ውስጥ ተካተዋል፡፡ በፓርቲው ከማእከላዊ ኮሚቴ አባልነት ተሰርዘዋል በሚል ከላይ የተገለጹት በድምሩ 51 የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት አቅርቧል፡፡



ለድምጽዎ የሚያምኑን

አድራሻ - ቦሌ ክፍላሚንን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ
+251 115 153468

ፋክስ
+251 115 510025

ፌስቡክ
/national-electoal-board-of-ethiopia-nebe

ትዊተር
@NEBEthiopia

ኢሜይል
contact@nebe.org.et

ድረ - ገጽ
www.nebe.org.et

ፓርቲው ከዚህ በላይ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ጉባኤውን የማያካሂድ ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀፅ 98 (1) መሠረት ከፖለቲካ ፓርቲ ምዝገባ እንደሚሰረዝ ቦርዱ አጥብቆ ያሳውቃል።

በመጨረሻም የፓርቲው ዋና ፀሀፊ አቶ ለገሠ ላንቃሞ፣ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዶ/ር አየለ አሊቶ፣ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ዘርፍ ኃላፊ አቶ ተገኝ ወልዴ እና የህግ ጉዳይ ኃላፊ እና የቁጥጥርና ኦዲት ኮሜቴ ሰብሳቢ የሆኑት አቶ መስፍን ኢያሱ በ2013 ጠቅላላ ምርጫ ወቅት ለብልጽግና ፓርቲ ቅስቀሳ ስላማድረጋቸው አቤቱታ የቀረበባቸው መሆኑ ይታወቃል። አቤቱታዎቹን መሠረት በማድረግ የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ለብልፅግና ፓርቲ በ6ኛው ሀገራዊ ምርጫ ወቅት ቅስቀሳ ማድረግ አለማድረጋቸውን በማጣራት ለቦርዱ እንዲያሳውቁ ቦርዱ ግንቦት 22/2014 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ አሳውቋል።

ፓርቲው ይህን ጉዳይ አስመልክቶ በቁጥር ሲአን/49/14 ለቦርዱ በጻፈው ደብዳቤ ዶ/ር አየለ አሊቶን ነጥሎ በማውጣት ግለሰቡ ከድርጅት ከተሰናበቱ አራት አመታት ያስቆጠረ በመሆኑ የቀረበባቸው ክስ አግባብነት የለውም ብሏል።

ቦርዱ ይህ ጉዳይ እንዲታይ ትዕዛዝ የሰጠው ለማዕከላዊ ኮሚቴ ሆኖ ሳለ የፓርቲው ዋና ጸሀፊ አለአግባብ የአንድ ግለሰብን ጉዳይ ብቻ አስመልክቶ ምላሽ መስጠታቸው አግባብነት የሌለው መሆኑን ቦርዱ ተመልክቷል። ስለሆነም የእነዚህ አራት አመራር አባላት ጉዳይ አሁንም ቦርዱ በግንቦት 22/2014 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ መሰረት የፓርቲው የማእከላዊ ኮሚቴ ጉዳዩን አስቀርቦ ማጣራት አድርጎ ማስረጃዎችን እንዲልክ ቦርዱ በጥብቅ ያሳስባል።

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር

ውብሸት አየለ ጌጤ
Woubshet Ayele Gete
Deputy Chairperson National Electoral Board